OFFICE OF ARTS & CULTURE
CITY OF SEATTLE

# የ2025 ዓ.ም ሥነ-ጥበብ በፓርኮች (Arts in Parks) መመሪያዎች

## የገንዘብ ድጎማው (Grant) አጠቃላይ እይታ

የሲያትል የሥነ-ጥበብ እና የባህል ጽሕፈት ቤት (ARTS) በመላ ከተማው በሚገኙ ፓርኮች የሚካሄዱትን የሥነ-ጥበብ እና ባህል ተኮር ዝግጅቶችን ለማሳደግ ከ2016 ዓ.ም ጀምሮ ከሲያትል ፓርኮች እና መዝናኛዎች (SPR) ጋር በሽርክና እየሰራ ነው። የከተማ አስተዳደሩ፣ ሥነ-ጥበብ በፓርኮች (Arts in Parks)፣ በተሰኘው ፕሮግራም ፣አማካኝነት በመላው ሲያትል በሚገኙ የተለያዩ ማኅበረሰቦች እየተከናወነ የሚገኘው ደማቅ ባህላዊ ሥራ ላይ ኢንቨስት ያደርጋል።

ይህ ፕሮግራም የአገልግሎት እጥረት እና ኢኮኖሚያዊ ጫና ከሚታይባቸው የከተማዋ አካባቢዎች በሚፈልቅ ሥነ-ጥበብ እና ባህል አማካኝነት የሲያትልን ፓርኮች ለማነቃቃት የሚሠሩ በአነስተኛ ደረጃ ያሉ ድርጅቶችን፣ ማኅበረሰብ ላይ የተመሠረቱ ቡድኖችን፣ እንዲሁም በግል የሚንቀሳቀሱ የሥነ-ጥበብ ባለሙያዎችን ይደግፋል። ይህ የገንዘብ ድጎማ የሲያትልን ብዝሐነት የሚወክሉ በታሪካቸው አገልግሎት የተነፈጉ ወይም የአገልግሎት እጥረት ከሚታይባቸው ማኅበረሰቦች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ሥነ-ጥበብ እና ባህላዊ ተሳትፎን የሚያስተዋውቁ፣ ብዝሐነትን የሚያከብሩ፣ እና በማኅበረሰቦች መካከል ግንኙነቶችን የሚገነቡ አዲስ እና ነባር ፌስቲቫሎች እና ዝግጅቶችን ይደግፋል።

ለማመልከት፣ የማመልከቻዎን ረቂቅ ግብረመልስ ለማግኘት፣ ብቁነትን በተመለከተ፣ ወይም ኦንላይን ቴክኒካዊ ድጋፍ ማግኘትን በተመለከተ መረጃ ወይም እገዛ አስመልክቶ ጥያቄ ካለዎት የገንዘብ ድጎማ ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ የሆኑትን Zach Frimmel በ(206) 963-9226 ወይም Zach.Frimmel@seattle.gov ያነጋግሩ።

**የአሜሪካ የምልክት ቋንቋን (በቪዲዮ በኩል) ጨምሮ በእርስዎ ቋንቋ ሊያነጋግሩዎት የሚችሉ አስተርጓሚዎች አሉን።** እርስዎ ብቻ ይደውሉልን እና የሚናገሩትን ቋንቋ ይንገሩን። የስልክ ጥሪውን የሚቀላቀል አስተርጓሚ እስክናገኝ ድረስ አጭር ቆይታ ሊኖር እንደሚችል ይገንዘቡ።

## ማመልከቻ

ማመልከቻዎን ኦንላይን በሲያትል ከተማ አስተዳደር የገንዘብ ድጎማ ድር ጣቢያ በኩል ያስገቡ፡-https://seattle.fluxx.io/user_sessions/new

ኮምፒውተር ወይም የኢንተርኔት ተደራሽነት የሌለዎት ከሆነ፣ ወይም ደግሞ ለማመልከት መሰናክል ሊሆንብዎት የሚችል ሌላ ማንኛውም ነገር ካለ፣ የገንዘብ ድጎማ ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ የሆኑትን Zach Frimmel ን በ(206) 963-9226 ወይም በZach.Frimmel@seattle.gov ያነጋግሩ።

## የማመልከቻ ማስገቢያ ቀነ-ገደብ

ማክሰኞ፣ ኖቬምበር 26፣ ቀን 2024 ዓ.ም 5 ፒ.ኤም (የፓሲፊክ ሰዓት አቆጣጠር) ላይ ነው

## የብቁነት/ መስፈርቶች

ይህንን የገንዘብ ድጎማ ለማግኘት ብቁ ለመሆን የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርብዎታል፡-

- በሲያትል የሚኖሩ ወይም በየጊዜው ሥራዎን በሲያትል የሚያቀርቡ ከሆኑ፣ በግል የሚንቀሳቀሱ የሥነ-ጥበብ ባለሙያ፣ አካባቢያዊ ድርጅት፣ ወይም ማኅበረሰብ ላይ የተመሠረተ ቡድን መሆን።
    - ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን፣ አካል ጉዳተኛ ሰዎችን፣ የስደተኛ እና ተፈናቃይ ማኅበረሰቦችን፣ እና የቀለም ማህበረሰቦችን ጨምሮ በሥርዓታዊ ጭቆና እጅግ የተጎዱ ማህበረሰቦችን የሚወክሉ ድርጅቶች እና በግል የሚንቀሳቀሱ የሥነ-ጥበብ ባለሙያዎች እንዲያመለክቱ ይበረታታሉ።
- የፌደራል ግብር ከፋይ መታወቂያ ቁጥር/Federal Tax ID number (Social Security Number/የማኅበራዊ ዋስትና ቁጥር (ITIN)፣ ወይም Employee Identification Number /የሠራተኛ መታወቂያ ቁጥር) ሊኖርዎት ይገባል።
    - አመልካች ቡድኖች በ501(c)(3) ሥር ለትርፍ ያልተቋቋሙ መሆን ወይም ደግሞ ፊስካል ስፖንሰር ወይም ፊስካል ወኪል መጠቀም አይጠበቅባቸውም።

በሚከተሉት ሁኔታዎች ሥር ለዚህ የገንዘብ ድጎማ ለማመልከት **ብቁ አይሆኑም**፡-

- ከዲሴምበር 31 ቀን 2024 ዓ.ም በኋላ የተከፈተ እና የግዜ ገደብ የሌለው የሥነ-ጥበብ በፓርኮች (Arts in Parks) ውል ካለዎት።

በዚህ የገንዘብ ድጎማ ተጠቃሚ ለመሆን **የእርስዎ ፕሮጀክት/ዝግጅት ብቁ የሚሆነው** የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ ነው፡-

- ፕሮጀክትዎ ጉልህ የሥነ-ጥበብ እና ባህላዊ ይዘቶችን ይኖረዋል።
- ፕሮጀክትዎ ለሕዝብ ክፍት እና ከክፍያ ነፃ ይሆናል።
- ለፕሮጀክቱ የዝግጅት መድህን ይኖረዋል።
- ፕሮጀክትዎ ለሲያትል ፓርኮች እና መዝናኛዎች (Seattle Park and Recreation ) ተልዕኮ መግለጫ (ለመጫወት፣ ለመማር፣ ለማሰላሰል፣ ማኅበረሰብ ለመገንባት፣ እና መሬቱን በተመለከተ ኃላፊነት የተሞላ አስተዳደርን ለማጎልበት የሚረዱ ጥሩ አቀባበል ያላቸው እና ደኅንነታቸው የተጠበቁ ዕድሎችን ለማቅረብ) ተገዥ ይሆናል።
- ፕሮጀክትዎ በሜይ 1 እና ኖቬምበር 30 ቀን 2025 ዓ.ም መካከል ባለው ጊዜ ብቁ በሆነ የሲያትል ከተማ ፓርክ ውስጥ ይካሄዳል።
    - *የተመራጩ ፓርኮች ዝርዝርን ይመልከቱ።*
    - በዳውንታዉን ወይም በሲቲ ሴንተር ፓርኮች ወይም በመጫወቻ ቦታዎች እና አረንጓዴ ቦታዎች ከማኅበረሰብ ማዕከሎች ጎን ለጎን በሚገኙ ላይ የሚካሄዱ ዝግጅቶች ለዚህ የገንዘብ ድጋፍ ብቁ ***አይደሉም***። *ብቁ ያልሆኑ ፓርኮችን ዝርዝር ይመልከቱ።*

ለዚህ ፕሮግራም በዓመት አንድ (1) ማመልከቻ ብቻ ማስገባት ይችላሉ።

## የገንዘብ ድጋፍ

የገንዘብ ድጋፉ አሸናፊዎች ለሚከተሉት ዓላማዎች ክፍያ የሚዉል የሥነ-ጥበብ በፓርኮች የገንዘብ ድጋፍ (በ2025 ዓ.ም ለሚካሄዱ ዝግጅቶች) ያገኛሉ፡- የሥነ-ጥበብ ባለሙያ ክፍያዎች፣ የማርኬቲንግ እና የማስተዋወቂያ ክፍያዎች፣ የፕሮጀክት ማኔጅመንት እና የሠራተኛ ወጪዎች፣ አቅርቦቶች፣ የመሣሪያ ኪራዮች ወይም ሌሎች ከምርት ጋር የተያያዙ ወጪዎች፣ አስፈላጊ የሆኑ ፈቃዶች፣ እና ከአጠቃላይ ድጋፉ መጠን 10 በመቶ በላይ ለማያስወጡ ከምግብ ጋር የተያያዙ ወጪዎች። በቅድሚያ በገንዘብ ድጎማ ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጁ ከፀደቁ ተጨማሪ ወጪዎች ሊፈቀዱ ይችላሉ። ለዚህ ፕሮግራም ምንም ዓይነት ከፊል የገንዘብ ድጋፍ የሌለ ሲሆን፣ ለ2024 የተመደበለት በጀት ላይ የተመሰረተ ነው። ከሥነ-ጥበብ በፓርኮች (Arts in Parks) የተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ከሌሎች የከተማ አስተዳደር የገንዘብ ድጋፍ ምንጮች ጋር ተዋህዶ ለተመሳሳይ ፕሮጀክት መዋል አይችልም።

አመልካቾች ለሚከተሉት የገንዘብ ድጋፍ ደረጃዎች ማመልከት ይችላሉ፡-

- $2,000
- $4,000
- $6,000
- $8,000

**የገንዘብ ድጋፉ ለሚከተሉት ጥቅም ላይ መዋል *የለበትም*፡-**

- ለሕዝቡ ተደራሽነት የሌላቸው እና ከክፍያ ነፃ ያልሆኑ ዝግጅቶት
- ሃይማኖታዊ አገልግሎቶች
- ገንዘብ ማሰባሰብን ዋና ዓላማ ያደረጉ ዝግጅቶች ወይም መግለጫዎች
- ስጦታዎች
- ከፕሮጀክቱ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ለሌላቸው የድርጅቶቹ አስተዳደራዊ ወጪዎች
- የመሳሪያ ወይም የሶፍትዌር ግዢ
- ከተፈቀደው አጠቃላይ የገንዘብ ድጋፍ 10 በመቶ በላይ ከምግብ ጋር ተያያዥ ለሆኑ ወጪዎች ማዋል አይፈቀድም

## የመረጃ ክፍለ ጊዜዎች

ይህንን የገንዘብ ድጎማ እና ማመልከቻ የማስገባት ሂደትን አስመልክቶ ተጨማሪ ነገሮች ይወቁ።

### የመረጃ ክፍለ ጊዜ 1 (ምናባዊ/ቨርቿል)

ሐሙስ፣ ኦክቶበር 24 ቀን፣ 2024 ዓ.ም
ምናባዊ/ቨርቿል፡- Microsoft Teams
እባክዎን ምላሽ ይስጡ

### የመረጃ ክፍለ ጊዜ #2 (በአካል)

ሰኞ፣ ኦክቶበር 28 ቀን፣ 6:00-7:30 ፒ.ኤም (በፓሲፊክ ሰዓት)

በአካል፡- Garfield Community Center
እባክዎን ምላሽ ይስጡ

**የማመልከቻ ረቂቅ ግብረመልስ ክፍለ ጊዜ**
በከተማ አስተዳደሩ ሠራተኞች እንዲገመገም የArts in Parks (ሥነ-ጥበብ በፓርኮች) ማመልከቻዎን ያጋሩ እና የመጨረሻ ማመልከቻዎን ከማስገባትዎ በፊት ረቂቁ ላይ ግብረመልስ ያግኙ።

**የማመልከቻ ረቂቅ ግብረመልስ ክፍለ ጊዜ 1 (ምናባዊ/ቨርቿል)**
ረቡዕ፣ ኖቬምበር 13 ቀን፣ 12:00-1:30 ፒ.ኤም (በፓሲፊች ሰዓት)
ምናባዊ/ቨርቿል፡- Microsoft Teams
እባክዎን ምላሽ ይስጡ

**የማመልከቻ ረቂቅ ግብረመልስ ክፍለ ጊዜ 2 (በአካል)**
ቅዳሜ፣ ኖቬምበር 16 ቀን፣ 10:00 ኤ.ኤም - 12:00 ፒ.ኤም
በአካል፡- Jefferson Community Center
RSVP